# Ethiopian Cultural Center in Belgium
# የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም

NEWSLETTER **ቁጥር 26 – July 04, 2021**

## ማውጫ Contents

**ዜና እረፍት፥ ክብርት ዶ/ር አበበች ጎበና ከዚህ አለም በሞት ተለዩ።** *በተለያዩ የበጎ ስራዎቻቸው የሚታወቁት አበበች ጎበና ዛሬ ጥዋት July 4, 2021 ዓም በ85 ዓመታቸው ከዚህ አለም በሞት መለየታቸው ታውቋል።*

**ገጽ 2-3**

==========================================================================

**Brief History of Ethiopia – Part 16: Menelik II: Architect of an Empire ዳግማዊ ምኒሊክ የአገር ግዛት አርክቴክት** Adwa victory brought Ethiopia new prestige and ensured the preservation of Ethiopian sovereign status. However, it did not completely remove a threat due to the ever-present European colonial powers occupying the entire Horn of Africa.

**ገጽ 3-6**

==========================================================================

**የስደተኛው ማስታወሻ** ቤልጅየም *ውስጥ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ከትውልድ አገሩ እስከ አውሮፓ ድረስ የሄደበት የግሉን የስደት ጉዞ የሚያትትበት አጭር መጣጥፍ ሲሆን ለሚቀጥሉት ተከታታይ ሳምንታት የሚቀርብ ይሆናል። በዚህ አጋጣሚ ጸሀፊውን በአንባቢዎቻችን ስም እጅግ አድርገን እናመሰግናለን።*

**ገጽ 7**

==========================================================================

**ሳምንታዊ የኮሮና ቫይረስ ሥርጭት፤ በቤልጅየም** በኮሮና ቫይረስ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር በመጠኑ እየጨመረ መምጣቱ ለጊዜው የተጠበቀ እና አሳሳቢ እንዳልሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያ ስቲቨን ቫን ጉኽት ተነናሩ። እንደርሳቸው ገለጻ የቁጥሮቹ መጨመር የበርካታ ምክንያቶች ጥ  ምረት ውጤት ሲሆን ዋና ዋና ምክንያቶች የሚባሉት በቫይረሱ አይነት (ዝርያ) ምክንያት እና ይልቁን ደግሞ በተወሰዱ የምርመራ ናሙናዎች ብዛት ናቸው።

**ገጽ 8-9**

==========================================================================

website https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium

## ዜና እረፍት፥ ክብርት ዶ/ር አበበች ጎበና ከዚህ አለም በሞት ተለዩ።



*በተለያዩ የበጎ ስራዎቻቸው የሚታወቁት አበበች ጎበና ዛሬ ጥዋት July 4, 2021 ዓም በ85 ዓመታቸው ከዚህ አለም በሞት መለየታቸው ታውቋል። በኢትዮጵያ ባህል ማዕከል ስም የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እየገለጽን አበበች ጎበና ሕፃናት ክብካቤና ልማት ማሕበር (አጎሕልማ) የተሰኘው ድርጅታቸውም ማረፋቸውን ባስታወቀበት የማህበራዊ ትስስር ገፁ ላይ ያሰፈረውን አጭር የሕይወት ታሪክ እንዳለ እናቀርባለን።*

ክብርት ዶ/ር አበበች ጐበና ፋሽስት ኢጣልያ ጦር ሀገራችንን በ1928 ዓ.ም በወረረበት ወቅት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ በግራር ጃርሶ ወረዳ በቶርበን አሼ ቀበሌ ገበሬ ማሕበር ሸበል አቦ በተባለች የገጠር መንደር ተወለዱ። በወቅቱ በነበረው ባህልና ልማድ ገና የ11 ዓመት ልጅ እንዳሉ ትዳር ለመያዝ ተገደዱ። ሆኖም የቀረበላቸውን የጋብቻ ጥያቄ በብቸኝነት በመቃወም ወደ አዲስ አበባ ገቡ። በአዲስ አበባ ስራን ሳይንቁ

ከግለሰቦች ቤት ከማገልገል እስከ ምርት ክፍል ኃላፊነት አገልግለዋል።

ክብርት ዶ/ር አበበች (እዳዬ) በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጭ ያሉ አብያተ ክርስትያናትን በማገልገል ከፍተኛ አበርክቶ ነበራቸው። በዚህም አጋጣሚ በ1972 ዓ.ም. ለመንፈሳዊ ጉዞ በሄዱበት በሀገራችን ተከስቶ በነበረው የተፈጥሮ ድርቅ ሳቢያ ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ሁለት ህፃናትን በመያዝ አበበች ጉበና ህፃናት ክብካቤና ልማት ማህበርን መሰረቱ። ክብርት ዶ/ር አበበች (እዳዬ) ባለፉት 41 (አርባ አንድ አመታት) ብዙ መቶ ሺህ ህፃናትን ተንከባክበው ለቁምነገር ያበቁ ሲሆን በተለያዩ ድህነት ቅነሳ ፐሮግራሞች ከአንድ ነጥብ አምስት ሚልዮን በላይ ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ሰተዋል። በመሆኑም በተለያዩ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ መድረኮች ታላላቅ ሽልማቶችና እውቅናዎችን እንዲሁም ከጅማ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ድግሪ በሰብአዊነት አግኝተዋል።

ክብርት ዶ/ር አበበች (እዳዬ) ድህነትን በተለይም የህፃናት ጉስቁልናን መቅረፍ የሚቻለው "በግለሰብ ደረጃ ለምፅዋት በሚወረወሩ ሽርፍራፊ ሳንቲሞች ሳይሆን በአንድነት በማበር እና ያለንን አቅም በማሳሰብ በችግር ላይ ያሉ ወገኖቻችንን በተለይም ሴቶችን ስናበቃ ነው።" የሚል እምነት ነበራቸው።

ሆኖም በቅርቡ በኮሮና በሽታ ምክንያት በጳውሎስ ሆስፒታል በጽኑ ህሙማን ክፍል ሲረዱ ቆይተው ዛሬ ጠዋት በተወለዱ በ85 ዓመታቸው ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል።

የእኚህ ደግ እና ሩህሩህ እናት ስራ ከመቃብር በላይ ገኖ ለዘላላም በአርአያነት በትውልድ ሲታወስ ይኖራል።

ለዘመድ አዝማዶቻቸው፤ ያለ እርሳቸው አለኝታ ላልነበራቸው ታዳጊ ሕፃናትና ልጆቻቸው ለዓላማቸው ደጋፊዎች እንዲሁም አጋሮች መጽናናትን እንመኛለን።

================================================================

**Brief History of Ethiopia – Part 16: Menelik II: Architect of an Empire**

Adwa victory brought Ethiopia new prestige and ensured the preservation of Ethiopian sovereign status. However, it did not completely remove a threat due to the ever-present European colonial powers occupying the entire Horn of Africa. It also represented a political and military disaster as Ethiopia was left without access to the sea. Menelik was also continuously troubled by attempts on the part of Britain, France and Italy to gain influence within the empire. But the emperor showed a remarkable skill for playing one superpower off against another.



website https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium

The European threat to the Ethiopian periphery worried Menelik II enough to order decade long military expedition to firm his grips on borderlands. Following the victory in Adwa up to 1906, Menelik focused on his military conquest of southern and western regions that would more than doubled the size of his domain. These regions were inhabited by nonhierarchical societies which practiced basic means of life and spoke non-Semitic languages. The superior weapons of the imperial forces and the hierarchical social organization enabled him to overwhelm and annex the Kingdoms of Kafa, Kembata, Walayta and Omotic-speaking peoples. It was during these campaigns that a force led by Ras Wolde Giyorgis (1851-1918) travelled southward to the shores of Lake Turkana (formerly Lake Rudolf) and raise the Ethiopian tricolour at the lake before returning to Kafa.

To the west, army units under the command of Ras Mekonnen established political control over Beni Shangul country while units led by Dejazmach Tesemma Nadaw (later Ras-regent to Lij Iyasu) proceeded through Illubabor and Gambella to establish imperial rule. The later might have facilitated the export of coffee via the fluvial route of Baro-Nile-Khartoum. The expansion reached all the extreme peripheries including most Borena – using a policy of either military confrontation or slow infiltration and effective political occupation.

In addition to the relentless expansion of his empire, Menelik also managed to bring some modernity to Ethiopia. He was said to be curious about everything especially machinery and technology. Everything he did to modernize Ethiopian indicate that the monarch was a progressive man. However, he saw no compelling reasons to alter his country's social order and bring a fundamental economic transformation. For example, he preferred to import manufactured goods into Ethiopia rather than methods of structuring the society that could facilitate the development of industrialization. European mode of production and/or its social structure could have brought a lasting social revolution as it did to the Japanese state.

The emperor introduced some measure of modernity to Addis



website  https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium

Ababa – stone buildings, bridges, paved streets, motorized vehicles and, to the imperial palace, piped water and electricity. He also set up a government post office which offered mail services adequate enough enable it to join the International Postal Union in 1908. This modernization derive also introduced services of telephonic and telegraphic communication systems which connected Addis Ababa with Italian-occupied Asmara (Eritrea) and French Djibouti. The first hotel was built (owned by Taitu, wife of Menelik II), the first Hospital opened and a government press established also during this period. Fiscal and judicial systems underwent internal reform and an unenthusiastic attempt was made to abolish slavery and slave trafficking, a mark which had soiled Ethiopia's image in the eyes of the world.

In 1905, the Bank of Abyssinia (an affiliate of the National Bank of Egypt) was founded in the capital, linking Ethiopia to the world's financial markets. There were relatively few skilled and educated Ethiopians who had significant roles in political and economic life of the country. Thus, the opening of the Menelik II school (Ecole Imperiale Menelik II) in Addis Ababa with Egyptian staff from the Orthodox Coptic church, a good example of the later concern for a compromise between tradition and innovation, was to fill this gap.

For the majority of Ethiopian population, the introduction of the symbols of modernization did not go beyond attracting their admiration to actually changing their lives. The only real innovation that touched many sectors of the society was the construction of the Djibouti-Addis Ababa railway which commenced in 1897, under the patronage of the French but mistrust of the British. During its building, the railway was the object of much controversy. An Anglo-French international rivalry led Menelik to boycott the use of its services and withdrawal Ethiopia from its construction. In 1902 for example, he refused to sanction the extension of the railway line to Harar. Thus, the first completed portion of the railway ran from Djibouti to a temporary depot in Ethiopia and stopped there just short of Harar. This terminus later evolved into the city of Dire Dawa. It was only in 1908 that France



website https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium

agreed that Ethiopia held sovereignty over the Ethiopian portion of the line. The construction of the rail link, nevertheless, was a historic milestone but Menelik II did not live to see the arrival of the railway in the capital in 1917.

A combination of unfortunate circumstances conspired to indicate that emperor Menelik II, "the rock of determination on which modern Ethiopia was built" was feeling the weight of time. He was unable to periodically travel to the provinces and several of his trusted advisers and confidants including Ras Makonnen and Alfred Ilg (his longtime adviser and foreign affairs consultant) died in 1906. Anticipating a breakout of internal conflict as the result of the weakening of the emperor's control over his kingdom, Britain, France and Italy signed the Tripartite Treaty, that defined their respective interests in Ethiopia. The July 1906 treaty allowed to France to administer railway and maintain a zone of influence in the Djibouti to Addis Ababa corridor. (A resulting, later treaty between France and Ethiopia led Menelik to consent to further extension of the railway line.) The Tripartite Treaty recognizes the overriding British interests in the Nile basin but what the Italians gained in terms of their interest to connect Eritrea with Italian Somaliland remained vague.

The division of Ethiopia by the three European colonial powers into economic spheres of influence is an example of neo-colonialism. Nonetheless, the signatories endorsed Ethiopia's national integrity and pledged their neutrality in the country's internal affairs. As usual, the ever-pragmatic Menelik gave little concessions away but witnessed his country benefit from the resulting socioeconomic changes.

Emperor Menelik II himself was apparently aware of the weakening of his political control because he announced the establishment a Council of Ministers and Ethiopia's first cabinet on 25 October 1907 to assist in the management of state affairs, thereby ensuring the continuity of the state.

*... to be continued*



website https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium

## የስደተኛው ማስታወሻ *ጸሀፊ ዳ.ሲ*

ነብስ አውቄ እስከማስታውሰው ድረስ ከኢትዮጵያ ውጪ የመኖር ፍላጎት ያደረብኝ ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ነው። ሀሳቡ የተጠነሰሰው ደግሞ ኒውዮርክ በምትኖረው የአባቴ አጎት ልጅ ወ/ሮ በቀለች አየለ አማካኝነት ነው። ወ/ሮ በቀለች በደርግ ዘመነ መንግስት የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበረው የአቶ ይልማ ካሳዬ ባለቤትና የደርጉ ቀኝ እጅ የነበሩት የፍቅረስላሴ ወግደረስ ዋና ፀሀፊመ ነበረች። ከዛም የተባበሩት መንግስታት ውስጥ ተቀጥራ ጀርመን ሀገር በሚገኘው ቢሮ ውስጥም ትሰራ ነበር። ከጥቂት ቆይታዋ በኋላ ቤተሰቧም ወደዛው ተዛውሮ አበረው መኖር ጀመሩ። ከአመታት የጀርመን ቆይታዋ በኋላ ደግሞ /Assistant Budget Secretary/ በመሆን ተሹማ ጡረታ እስከወጣችበት ጊዜ ድረስ አገልግላለች።

1996 ዓ.ም. ላይ ወደ ኢትዮጵያ መጥታ በነበረችበት ጊዜ ወላጅ አባቴ አቶ ሲሳይ ተድላ የሁልጊዜ ጥያቄውን ያቀርባል።" እባክሽ ይህን ልጅ እንደው ለዘሬ እንኳን እንዲተርፍ አንቺ ጋር ወስደሽ አስተምሪልኝ" ይላታል።እርሷም የተለመደውን የ"እሺ,ታ" መልሷን ሰጥታው ነበር። በዛን ጊዜ እኔ በኩዊንስ ኮሌጅ የመጀመሪያ ዓመት የህግ ተማሪ ነበርኩ። የትምህርታ ዕድል / Scholarship/ ዕድል ላገኝ የምችልበትን ሁኔታ እንደምታመቻች ነግራኝ ብዙም ባይሆን ብላ አንድ ሺ ብር ሰጥታኝ ወደመጣችበት አሜሪካ ተመለሰች። ከዛማ የውሃ ሽታ ሆና ቀረች።

1998 ዓ.ም. ይህንኑ ከኢትዮጵያ ውጪ የመኖር ፍላጎቴን ሊያሳካ የሚችል የሆነ አጋጣሚ የተፈጠረልኝ መሰለኝ።አንድ ባለሀብት ነኝ ባይ ሰው ጋር ተዋወቅን። እናም በሱዳን የተለያዩ ከተሞች የሙዚቃ ስራዎችን ለማቅረብ የሆነ የሙዚቃ ቡድን ማቋቋም እንደሚፈልግ ገለፀልኝ። ኢትዮጵያ ቴሌቭዥን በምሰራበት ጊዜ አውቃቸው የነበሩ ተወዛዋዥ እና ድምፃውያንን፤ እርሱም ያውቃቸው ከነበሩ ድምፃውያን ጋር አድርገን አንድ ቡድን መሰረትንና በእርሱ መኖሪያ ቤት ማስጠናት ጀመርን። የእኔ ዋና ግብ ከሱዳን ወደ አሜሪካ ማቅናት፣ የሙዚቃ ቡድኑ ደግሞ ሱዳን የመንና ዱባይ የሙዚቃ ስራዎችን አቅርቦና ሸቅሎ መመለስ ነበር ዋነኛ አላማው።እንደታሰበው ሳይሆን ግን ይቀራል። እኔም ለአባቴ ወደ አዲስ አበባ ደውዬ ለአጎቱ ልጅ አሜሪካ ደውሎ ያለሁበትን ሁኔታ እንዲያስረዳትና የሱዳን ስልክ ቁጥሬን እንዲሰጣት አደረኩኝና በቀላሉ በስልክ ስለሁኔታዬ ለማስረዳት ቻልኩ። በሱዳን የሚገኘው የተባበሩት መንግስታት ስደተኞች ቢሮ ውስጥ የምትሰራ እጅጋየሁ የምትባል ጓደኛ ስላለቻት በእርሷ አማካኝነት አስፈላጊውን የስደተኝነት ማመልከቻዬን ለማቅረብና ተቀባይነት እንዳገኝ እንደምታደርግ ነገረችኝ። የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ይህች ሰው ቤተሰቦቿን ለመጠየቅና ለአንድ ወር እረፍት አሜሪካን ሀገር እንደሆነችና ከእረፍት እንደተመለሰች ጉዳዬን እንደምታስተካክልልኝ ነገረችኝ።

ይቀጥላል,,,,,,

**ቤልጅየም - ሳምንታዊ የኮሮና ቫይረስ ሥርጭት፤**

(ምንጭ: የማህበረሰብ ጤና ሳይንስ ተቋም - Sciensano)

በወር ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በኮሮና ቫይረስ የተያዙ ሰዎች ቁጥር ጨመረ። ባለፈው ሳምንት በቫይረሱ የተያዙት ሰዎች ቁጥር በአማካይ **በ5 በመቶ የጨመረ** መሆኑ ታውቋል። የተጓዦች ቁጥር በሚያስደንቅ ሁኔታ መጨመር እና ከዚያም የተነሳ ምርመራ የተደረገላቸው ሰዎች መብዛት እንደምክንያት ተወስደዋል።

በቤልጅየም የማህበራዊ ጤና ሳይንስ ተቋም በሳምንቱ መጨረሻ የዘገበው መረጃ የሚከተለው ነው።

- ከJune 23 እስከ June 29 ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ በየቀኑ በአማካይ **378** ሰዎች በኮሮና ቫይረስ እንደተያዙ ታውቋል። ይህ ከሳምንት በፊት ካለው አሃዝ ጋር ሲነጻጸር **በ5 በመቶ** መጨመሩን ያሳያል። በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር ሲጨምር ባላፈው አንድ ወር ውስጥ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው። በዚህም መሠረት ወረርሽኙ ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ በምንኖርባት አገራችን በአጠቃላይ **1,086,508** ሰዎች በቫይረሱ መያዛቸው ተረጋግጧል።

- በአጠቃላይ በአሁን ሰዓት **271** የኮሮና ቫይረስ ህመምተኞች በተለያዩ ሆስፒታሎች ውስጥ በህክምና እየተረዱ ይገኛሉ። ይህ ቁጥር ከባለፈው ሳምንት ጋር ሲነጻጸር **በ29 በመቶ** ቀንሷል።

- በየሆስፒታሎቹ ካሉት የኮቪድ-19 ህመምተኞች ውስጥ **123** ታማሚዎች በጽኑ ሕሙማን ክፍል በከፍተኛ እንክብካቤ ላይ ይገኛሉ። ከባለፈው ሳምንት አንጻር ሲታይ ወደዚህ ክፍል መግባት ያለባቸው ህመምተኞች ቁጥር **በ22 በመቶ** ቀንሷል። ከጽኑ ህሙማን ውስጥ ሰው ሰራሽ የመተንፈሻ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቁጥር **83** ሲሆን ካለፈው ሳምንት ጋር ሲነጻጸር **በ18 በመቶ** ቀንሷል።
- **ሆስፒታል የሚገቡ:** ከJune 25 እስከ July 1 ድረስ በየቀኑ በአማካይ **16** ሰዎች በኮቪድ-19 ምክንያት ሆስፒታል ገብተዋል። ይህ ቁጥር ካለፈው ሳምንት ጋር ሲነጻጸር **በ40 በመቶ** ቀንሷል።
- **የሟቾች ቁጥር:** ከJune 23 እስከ 29 በነበረው ሳምንት በኮሮና ቫይረስ ምክንያት በየቀኑ በአማካይ **4** ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል። ይህ ቁጥር ከባለፈው ሳምንት ጋር ሲነጻጸር **በ31 በመቶ** ቀንሷል። በዚህ መሰረት በምንኖርባት አገራችን አጠቃላይ የሟቾች ቁጥር **25,185** ደርሷል።
- እስከ June 25 ድረስ በቤልጅየም ውስጥ **7,251,205** ሰዎች ቢያንስ የመጀመርያውን ክትባት ወስደዋል። ይህ **77.9 በመቶ** የሚሆነው የጎልማሳ

ህዝብ ቁጥር ነው። ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ጨምሮ ከአጠቃላይ የህዝብ ብዛት አንጻር ሲታይ ደግሞ ይህ ወደ **62.9** በመቶ ይደርሳል። ከእነዚህ ውስጥ **4,073,334** ሰዎች ሁለተኛውንም ክትባት ስለወሰዱ ሙሉ በሙሉ ተከትበዋል ማለት ነው።

## ማጠቃለያ (እስከ July 2, 2021)

| የሰው ቁጥር | በጠቅላላ | ባለፉት 7 ቀናት (በየቀኑ አማካይ) | ባለፉት 14 ቀናት (በየቀኑ አማካይ) |
|---|---|---|---|
| የህመምተኞች | 1.1 ሚሊዮን | 378 (+5%) | 369 (-56%) |
| የሟቾች | 25,200 | 4 (-31%) | 5 (-46%) |
| ሆስፒታል የገቡ | 75,400 | 16 (-40%) | 21 (-54%) |
| ምርመራ የተደረገላቸው | 15.4 ሚሊዮን | 47,100 (+23%) | 42,700 (+4%) |
| አንድ ጊዜ የተከተቡ (>18 ዓመት) | 7.3 ሚሊዮን | 83,900 (-12%) | 89,500 (+16%) |

## ተያያዥ ዜና፥

በኮሮና ቫይረስ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር በመጠኑ እየጨመረ መምጣቱ ለጊዜው የተጠበቀ እና አሳሳቢ እንዳልሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያ ስቲቨን ቫን ጉኽት ተነናሩ። እንደርሳቸው ገለጻ የቁጥሮቹ መጨመር የበርካታ ምክንያቶች ጥምረት ውጤት ሲሆን ዋና ዋና ምክንያቶች የሚባሉት በቫይረሱ አይነት (ዝርያ) ምክንያት እና ይልቁን ደግሞ በተወሰዱ የምርመራ ናሙናዎች ብዛት ናቸው።

በመጀመሪያ ደረጃ የምርመራዎች ብዛት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ስለሆን ተመርምረው የማያውቁ የማህበረሰቡ ክፍሎች (ወጣቶች) በብዛት እየተመረመሩ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በጣም ተላላፊ የሆነው ኮሮና ቫይረስ ዴልታ የሚባለው (መጀመርያ ህንድ ውስጥ የተከሰተው ዝርያ) እየጨመረ መምጣቱ ታውቋል። ይህ ዝርያ በአሁን ሰዓት ቤልጅየም ውስጥ ካሉት ዓይነቶች ከአንድ አራተኛ በላይ የሚሆኑትን የያዝ ሲሆን በሚቀጥሉት ሳምንቶች ውስጥ ይጨምራል ተብሏል።

ሆኖም ግን በቫይረሱ ምክንያት ሆስፒታል መግባት ያለባቸው ሰዎች ቁጥር እየቀነሰ እስከሄደ ድረስ ምንም የሚያሳስብ ነገር እንደሌለ ሃላፊው ጨምረው ተናግረዋል።

==========================================================================



website https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium

# Ethiopian Cultural Center in Belgium
# የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም

## የኢትዮጵያ የኮቪድ 19 ስርጭት




27/06/2021 በተደረገ 3,334 የላቦራቶሪ ናሙና ምርመራ 54 ሰዎች በኮሮና ቫይረስ መያዛቸው ተረጋግጧል። በአጠቃላይ እስካሁን በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 275,935 ደርሷል። በሌላ በኩል 553 ሰዎች ከበሽታው ያገገሙ ሲሆን በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ 259,044 ሰዎች ከበሽታው አገግመዋል።




ባለፉት 24 ሰዓታት ውስጥ በተደረገ 4,440 የላቦራቶሪ ናሙና ምርመራ 45 ሰዎች በኮሮና ቫይረስ መያዛቸው ተረጋግጧል። በአጠቃላይ እስካሁን በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 276,368 ደርሷል። በሌላ በኩል 150 ሰዎች ከበሽታው ያገገሙ ሲሆን በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ 260,949 ሰዎች ከበሽታው አገግመዋል። በሁለቱም ሰንጠረዦች እንደምትመለከቱት የኮቪድ19 ስርጭት እየቀነሰ ነው ነገር ግን የተለመደው ጥንቃቄ አይለየን።

መልካም ንባብ መልካም ሳምንት

website https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium